# ወያኔን በማይገባው ቋንቋ ለመፋለም

ከመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ የሥነ ጽሑፍ ዝግጅት ክፍል የቀረበ

" የኢተፖድህ ስልት ለሕዝባችን ትግልና መስዋዕትነት ጀርባ አንስጥ የሚል ስልት ነው።" በማለት የኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት (ኢተፖድህ) በቀስተ ደመና ሬዲዮ ያስተላለፈውን መግለጫ በጥሞና አዳምጠነዋል። እኛም ከዚህ በላይ በቋጠርነው ርዕስ ተንተርሰን የሚከተለውን ልናክልበት እንሻለን።

በመስከረም ወር 1992 ዓ.ም. በፍራንክፈርት ከተማ በተካሄደው የኢተፖድህ ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የግንቦቱን የወያኔ ምርጫ በማስመልከት፣ የሚችሉ ዴሞክራቶች ሁሉ ተመዝግበው በምርጫው እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያስተላለፈው ጥሪ ከዚህ የወያኔ የተጭበረበረ ሂደት ሕዝባዊ ትግል እንጂ፣ በግንቦት ማግስት የምርጫ ድል ይፈልቃል ከሚል የተሳሳተ ዕምነት በመነሳት ያልነበረና፣ አላማውም በዚህ የምርጫ እንቅስቃሴ ሳቢያ ለድሕረ ግንቦቱ ሕዝባዊ ትግል አዲስ እምርታ ለመፍጠር ነበር።

እንዳለውም ሁሉ ታዲያ! በዚህ የምርጫ እንቅስቃሴ ሳቢያ ዛሬ በሐገራችን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዳር እስከዳር የሚያንቀሳቅስ ሕዝባዊ እምርታ እየተፈጠረ ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች አንገብጋቢና አጣዳፊ ተግባር ይህ ሕዝባዊ እምርታ በምርጫ እንቅስቃሴ አስታኮ የተከሰተ እምርታ እንደመሆኑ መጠን በግንቦት የወያኔ የጊዜ ሰሌዳ ተወስኖ፣ በምርጫው ማግስት ቀስ በቅስ እንዳይከስም የተቻለውን ሁሉ ማድረግ እንደሆነ ግልጽ ሆኖ ይታየናል።

ድሮም ቢሆን ትኩረታቸው ከምርጫው በሚገኘው ወንበር ላይ ሳይሆን፣ ከምርጫው ዕንቅስቃሴ በሚፈልቀው ሕዝባዊ ትግል ላይ የሆነ፣ የሐገራችን ዴሞክራቶች ይህ የተከሰተው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ከመክሰም ይልቅ እንዲሰፋና እንዲያይል በዓይናቸው ስር ስለሚካሄደው ትግል የጋራ እይታ፣ ስለቀጣዩ ትግል ይዘትና እቅጣጫ የጋራ ራዕይ እንደሚያስፈልጋቸው ግልጽ ነው። ይህንን ጥራት ያለውን ትግል አጋዥ የጋራ አቋም ለመያዝ ከተፈለገ ደግሞ ለአንዲት ሰከንድም እንኳን ቢሆን የድህረ ግንቦቷን አገራችንን በአእምሯቸው መቃኘት ይኖርባቸዋል። የግንቦቱ ምርጫ የሰጠውን ውጤት ሰጠ አገራችን ከነአስር ሺህ እስረኞቿ፣ ከነሚሊዮን ረሐብተኞቿ፣ ከነዘፈቀደ አገዛዟ፣ ከንአፋኝ ካድሬዎቿ፣ ሕዝብን ከሕዝብ ለማናከስ ሆን ተብለው ከተቀበሩ ቦንቦቿ ጋር ትቀጥላለች። ከግንቦት በኋላም ጭቆናም ትግልም ይቀጥላሉ። በእኛ በኩል ይህ ትግል ይቀጥል፣ ዛሬ የተነሳሰው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ይፋፋም፣ ይስፋፋ ይቀናበር ማለት ብቻ ሲሆን፣ ለትግል ራዕያቸው ጥራት ሲባል ለዚህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አስፈላጊውን ትኩረትም ሆነ ቅድሚያ ከማይሰጡ ሁለት አቅጣጫዎች መጠንቀቅ ያስፈልጋል እንላለን።

የመጀመሪያው አቅጣጫ፣- ፓርላሜንት ወንበር ብዛት ላይ ትኩረቱን ያነጣጠረ፣ ካለፈው ምርጫ ይበልጥ ወንበር ተገኝቷል በሚል አጉል ድል ለመግደርደር የሚሞክር፣ ለዚህ ሕዝባዊ ትግል ጀርባ ሰጥቶ ወያኔ በሚፈቅደው ፓርላሜንታዊ ተቃውሞ እራሱን አጥሮ የሚቀመጥ አቅጣጫ ይሆናል። ይህ አቅጣጫ ግን ዴሞክራሲ ባልሰፈነበት፣ የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ተጋድሎ ገና የሚጠበቅበት አመቺ የሃይል ሚዛን ባልተፈጠረበት ስለሚደረጉ የተጭበረበሩ ምርጫዎች ምንነት ያልተረዳ፣ ወይም ራሱን የሚያታልል አቅጣጫ ነው። በሐገራችን ይካሄዳል የሚባለው የወያኔ ምርጫ የተባበሩት መንግሥታት የምርጫ ኤክስፐርቶች በሰጡት የለሰለሰ መጠሪያ መሠረት "ሪዘልት ኦርኤንትድ" ወይም ሆን ተብሎ ከጥንስሱ አንድ የተፈለገ ውጤት ለማምጣት የሚካሄድ የምርጫ ሂደት ነው። ዴሞክራሲ የለምና የሚገኘው ውጤት በምንም ዓይነት የሕብረተሰቡን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ውጤት አይሆንም። በነገው የወያኔ ፓርላሜንት ውስጥ የሚኖሩ ተቃዋሚዎች ቁጥር ከወዲሁ በወያኔ የተወሰነ ቁጥር ነው። ሕዝብ ለማደናገር፣ ተቃዋሚዎችን ለመከፋፈል፣ ነፃ ምርጫ ተካሂዷል ብሎ ለማጭበርበር የሚያስፈልገውን ያህል ሃያም፣ አምሳም፣ ከዚያም በላይ ተቃዋሚ ፓርላሜንት እንዲገባ ይደረጋል። ይህንን ለማድረግ የሚያደፋፍረው ደግሞ ከላይ እንዳልነው የ "ሪዘልት ኦርየንትድ" ወይም ሆን ተብሎ ከጥንስሱ አንድ የተፈለገ ውጤት ለማምጣት የሚካሄድ ምርጫ ሌላው ገጽታ ነው። ምርጫ አዘጋጁ መንግሥት በፓርላሜንቱ ውስጥ የተቃዋሚዎችን

ቁጥር በመወሰን ብቻ አይመለስም። በፓርላሜንቱ ውስጥ የሚኖረውን ተቃውሞ ልክም፣ መጥኖ፣ ለክቶና አጥሮ የሚወስነው ያው ፀረ ሕዝቡ መንግሥት ነው። የአገችን ዴሞክራቶች ከዚህ ወያኔ ከሚፈቅደው ልክ ከማያልፍ ተቃውሞ ይልቅ ወያኔ በማይፈቅደው፣ በማይወደው፣ ግራ በሚጋባበትና ከጦር በሚፈራው የኢተፖድህ መግለጫ እንዳለውም በኢትዮጵያ መንደሮችና ከተሞች፣ መንገዶችና ገጠሮች በሚካሄደው ትግል ላይ አተኩረው የሕዝባችንን የተቃውሞ ትግል ማገዝ፣ ማፋፋምና ማስተባበር ይጠበቅባቸዋል።

ሁለተኛው አቅጣጫ፣- የሕዝባችን ትግል ገና ባለማየሉና ባልቀነባበሩ ነፃ ምርጫ ስላልተደረገ የተገኘውን ውጤት እንደሽንፈት የሚቆጥር፣ ከዚህም ተነስቶ በወያኔ ሥር ነፃ ምርጫ ስላልተካሔደ ብቻ ባለፉት ወራት የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ ትግልና የተከፈለውን መስዋእትነት ችላ ብሎ ወያኔን በሚገባው የትጥቅ ቋንቋ ለማነጋገር፣ ለሕዝባዊው ትግል ትኩረት መስጠት የማይፈልግ አቅጣጫ አለ። በኛ በኩል ዱሮም ቢሆን እዚህ ምርጫ እንቅስቃሴ ውስጥ "ሁሉም ይሳተፍ" በማለት መስከረም ላይ ኢተፖድህ ያደረገው ጥሪ በስምንት ወር ውስጥ ወያኔ በምርጫ ተሸንፎ፣ በስምንት ወር ውስጥ በዚህ ሕዝባዊ ንቅናቄ ሳቢያ ሃገራችን ደሞክራሲ ሰፍኖ፣ ኢትዮጵያችን ማርና ወተቱ ጣዕሙ የሚጨምርባት አገር ትሆናለች ከሚል እምነት ተነስቶ ~~እንዳልሆነ ከምርጫው የተረዳነውን ያህል~~፣ ትኩረቱ በምርጫው ውጤት ላይ ሳይሆን፣ በምርጫው እንቅስቃሴ ሳቢያ በተነሳሳው ሕዝባዊ ትግልና ከሱም በሚቀሰመው በምንም ዓይነት አሳሳችነት በሌለው ትምሕርት ላይ መሆን እንዳለበት ግልጽ ይመስለናል።

ባለፉት ወራት ወያኔ ካድሬዎች በመርበትበት የተነሳ ለትግል በተነሳሳው ሕዝባችን ላይ የፈጸሙትን ግፍና የተከፈለውን መስዋዕትነት ስንመለክት የምንቀስመው መሠረታዊ ትምሕርት ወያኔን በሚገባው ቋንቋ ሳይሆን፣ በማይገባው፣ በማያውቅበት፣ በማይፈቅደው፣ በሚፈራውና ግራ በሚጋባበት ሕዝባዊ የፖለቲካ ትግል ለመፋለም የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና የኢትዮጵያ ሕዝቦች አስፈላጊ የሆነው ወኔውም፣ ፈቃዱም፣ ብቃቱም አላቸው የሚል ትምሕርት ነው።

ዛሬ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች አጣዳፊና አንገብጋቢ ተግባር በዚህ ሕዝባዊ ወኔና የትግል ብቃት ላይ የመገንባት ተግባር ነው። ይህንን ካላወቁበት ከግንቦት ማግስት ይህ ህዝባዊ ትግል ሰብሳቢና አቅጣጫ ሰጭ አጥቶ ለረጅም ጊዜ ሊከስም ይችላል። የሐገራ ችን ዴሞክራቶች በግንባር ቀደምነት ቀስቅሰው ያቀጣጠሉትን ትግል ቀጣይነት ለማረጋገጥ ስልት መቀየስ ካቃታቸው ከትግሉ ጊዜያዊ መክሰም ጋር ተያይዞ ሊመጣ የሚችለው አደጋ ለሁሉም ግልጽ ሊሆን ያስፈልጋል። ቀጣይ ትግል ከሌለ በመቶ ሺህ እየተቆጠሩ የወያኔ ካድሬዎች ዓይን ውስጥ የግቡት ወገኖቻችን የወያኔ የምርጫ ሰሞን "ደሞክራሲ" ባከተመ ማግስት ለነዚሁ ካድሬዎች ቀጣይና የባሰ ፈተና፣ ለነዚሁ ካድሬዎች ቀጣይና የባሰ ግፍ፣ ለነዚሁ ካድሬዎች ቀጣይና የባሰ እንግልት የሚጋለጡበት ሁኔታ ይኖራል። ይህ ከሆነ ደግሞ ሕዝባችን መጨረሻው ለማይታይ ረዥም ጊዜ መልሶ ተስፋ መቁረጥ ባሕር ውስጥ የሚዘፈቅበት፣ በተቃዋሚ ኃይሎች ቅንጣትም ትሁን አመኔታ የሚያጣበት፣ ከወያኔ በስተቀር ለሁሉም አስቸጋሪ የሆነ ሁኔታ ይፈጠራል።

ይህ የሚሆነውም የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች በንቅናቄው ሃያልነት ተዘናግተው። ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያስፈልገውን በሐገር አቀፍ ደረጃ የማስተባበርና የማስተጋገዝ ተግባር ሲረሱና በሚጠይቀው ፍጥነት ለመተግበር ሲሳናቸው ብቻ ስለሆነ፣ ብሔራዊና ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት እንዲነሳሱ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

መኢሶን
የሥነ ፅሁፍ ዝግጅት ክፍል.

[illegible]
ሚያዝያ 20 ቀን 1992 ዓ.ም